ትግራይ ዴሞክራሲያዊ ፓርቲ (ት. ዴ. ፓ)
Tigray Democratic Party (T.D.P)

በወቅታዊ ሀገራዊ ሁኔታ ላይ ከትግራይ ዴሞክራሲያዊ ፓርቲ (ትዴፓ) ማዕከላዊ ኮሚቴ
የተሠጠ መግለጫ

ሀገራችን ኢትዮጵያ ከውስጥም ከውጭም ጠላቶች የተጋረጡባት እጅግ ፈታኝ ሁኔታ በወጉና በጥልቀት የምንረዳ ሲሆን በዚህም ምክንያት የአገራችን ህዝብና የኢፌድሪ መንግሥት ይሽንን አደጋ ለመቀልበስ እየወሰዱት ያሉ እርምጃ የምንደግፍ መሆኑን እናረጋግጣለን። እንዲሁም የኢትዮጵያ መከላከያ ሠራዊትና የክልል መንግስታት ልዩ ኃይሎች ጁንታውን ለመደምሰስ እየከፈሉት ያሉትን ከፍተኛ ሀገራዊ መስዋእትነት የምንደግፍና ለዚህም ታላቅ ልባዊ ክብር የምንሠጥ መሆኑን እንገልፃለን።

ጁንታው እና አሸባሪው ህወሓት አመራር ኢትዮጵያን ለማፈራረስና ብሎም ትግራይን ለመገንጠል እያካሄደ ያለው አፍራሽ ድርጊት መወገዝ ያለበት ሲሆን፣ ይሽንንም የዚህ መሠሪ ቡድን ኢትዮጵያን የማተራመስ ተግባር እያወገዝን ሁሉም የትግራይ ህዝብም ሀገሩን ኢትዮጵያን ለመታደግ ከኢትዮጵያ መከላከያ ሠራዊት ጋር በመሠለፍ አሸባሪውን ህወሓት ላንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ከራሱ ጀርባና ከኢትዮጵያ ምድር ነቅሎ ለመጣል በሚደረገው ትግል ከሌላው ኢትዮጵያዊ ጋር እንዲሠለፍ እናሳስባለን። ሽብርተኛው ህወሓት ሲመታ ህዝቡ ተመታ ብሎ የሚያላዝነው የማደናገር ፕሮፖጋንዳ ውኃ የማይቋጥርና የትግራይ ወጣትና ህዝብም ጦርነቱ ፀረ-ጁንታ እንጂ ፀረ-የትግራይ ህዝብ አለመሆኑ መገንዘብ አለበት።

ልሂቃንና ፖለቲካ መሪዎች አገርን የመታደግ፣ ህዝብን የማስተባበር እና አንድነትን የማጠናከር ከፍተኛ ኃላፊነት ተጥሎባቸዋል። በዚህም እሳቤ አሁን የገጠመንን ፈታኝ ሁኔታ በሰከነና በበሰለ ፖለቲካዊና ሁለመዳያዊ አመራር ልንፈታው ይገባል። ስለሆነም ሁሉም ልሂቅና አመራር ህዝብን ከህዝብ ጋር ከሚያጋጭ፣ የአገርን አንድነት ከሚንድ እና የመከላከያ ሠራዊትን ክብር ከሚያዋርድ ንግግር እና እሳቤ መቆጠብ አለበት እንላለን። በተለይም አንዳንድ ጥቂት የአማራ ልሂቃን የትግራይና የአማራ ህዝቦችን ለማጋጨት ስሑት መግለጫ ከመስጠት እንዲቆጠቡ እናሳስባለን።

ከሰኔ 21፣ 2013 ዓ/ም ጀምሮ በመላው ኢትዮጵያ ተጋሩን የማሠር፣ የንግድ ድርጅቶቻቸውን የመዝጋት እና የማወከብና የማንገላታት ሁኔታዎች እያጋጠሙ እንደሆነ የኢትዮጵያ ሠብአዊ መብቶች ኮሚሽን (ኢሠመኮ) ባወጣው መግለጫ ላይ የተመለከትን ሲሆን እንዲሁም ከተለያዩ ምንጮች ፓርቲው ሊያረጋግጥ ችሏል። ማንኛውም ሠው አሸባሪው የህወሓት አመራርን ሲደግፍ ከተገኘ በሕግ ሊጠየቅ እንደሚገባ ትዴፓ በፅኑ ያምናል፤ ለዚህም ተግባራዊነት ከመንግሥት ጎን ይሰለፋል። ሆኖም ግን ከሕግ አግባብ ውጭ የሚፈፀሙ የዜጎች እስር፣ የድርጅቶች መዝጋትና ወከባና እንግልት ትዴፓ በፅኑ ይቃወመዋል፤ በአስቸኳይ እንዲታረምም መንግሥትን ይጠይቃል። በተለይም በታችኛው የፀጥታ መዋቅር የሚፈፀሙ ከሕግ አግባብ ውጭ ተጋሩን ለይቶ የማሰር፣ ድርጅቶችን የመዝጋት፣ ጊዜያዊ ጥቅምን ማዕከል ያደረጉ ወከባና እንግልት በአስቸኳይ እንዲታረሙና ይሽንን ኢሕጋዊ ተግባራት በንፁሃን ተጋሩ የሚፈፅሙ አንዳንድ የፀጥታ እና መስተዳድር አካላት ላይ ሕጋዊ እርምጃ እንዲወሰድ ትዴፓ በፅኑ ያሳስባል።

በህግ ጥላ ያሉ ዜጎችም ሰብአዊ፣ ሕገመንግስታዊና ዜግነታዊ መብቶቻቸው ተከብረው በወጉ እንዲያዙ እና ፍርድ ቤት ቀርበው ጉዳያቸው እንዲታይ እንዲደረግ ትዴፓ ይጠይቃል። እንዲሁም በወንጀል የማይፈለጉና በስህተት የታሰሩ ዜጎችን አጣርቶ ባስቸኳይ የመፍታት ሂደት እንዲፋጠን እንጠይቃለን። በተጋሩ ላይ የሚወሠዱ ህግን ያልተከተሉ የሙበት ጥሠቶችና ወከባዎች አሸባሪውን የጁንታ አመራር የሚጠቅምና የሚያጠናክር መሆኑ ግንዛቤ መወሠድ አለበት።

የወልቃይትና የራያ መሬቶችን በተመለከተ በሕገ መንግስቱ እና በህዝቡ ውሳኔ መሰረት እንዲሁም ኢትዮጵያዊነት ሕበር ቀለማትን በሚያደምቅ መልኩ እንዲፈታ ትዴፓ እምነቱን ይገልፃል። ጨዋውና ደጉ የኢትዮጵያ ህዝብም እንደ ጥንት ጥዋቱ ባካባቢው ላሉ ህጋዊ ተጋሩ ዜግነታዊ መብቶቻቸው ተከብረው በኢትዮጵያዊነታቸው ኮርተው እንዲኖሩ በማድረግ የተለመደው ትብብርህን እንጠይቃለን። እንዲህ በመደረጉ ጁንታው የሚያልመውን ትግራይን የመገንጠልና ኢትዮጵያን የማጉደል እኩይ ተግባር ለማኮላሸት ትልቅ ሚና እንደሚኖረው ትዴፓ ያምናል።

የኢትዮጵያዊያን ዳግማዊ ዓድዋ ድል እና ከፍታችን የሆነውን ታላቁ የህዳሴ ግድብ የውጭና የውስጥ ጠላቶቻችንን ተቋቁመን ሁለተኛው ሙሌትን በሚያስተናግድ መልኩ በኢትዮጵያዊያን ተገንብቶና መንግስታችንም ባሳየው ከፍተኛ የአመራርና ዲፕሎማሲ ልሕቀት ወደ መጠናቀቁ ደርሷል። በመሆኑም ትዴፓ የተሰማውን ደስታ እየገለፀ አሁንም ጀግናው የኢትዮጵያ ህዝብ ግድባችን እስኪጠናቀቅ ድረስ ማድረግ የሚገባውን ቁሳዊ፣ ገንዘባዊና ሞራላዊ ድጋፍ በማድረግ ከመንግስታችን ጎን እንዲቆም ትዴፓ ይጠይቃል።

የትዴፓ ማዕከላዊ ኮሚቴ

አዲስ አበባ ------- ሐምሌ 12፣ 2013 ዓ/ም

ስልክ ቁጥር +251-118-65-13-36/+251-940-79-08-22/+251-914-73-35-39
Website: tigraydemocraticparty.com, email: tigraydemocraticparty@gmail.com
ልደታ ክፍለከተማ፣ ወረዳ 03፣ ፖፖሲኖስ ሕንፃ 3ኛ ፎቅ፣ የቢ.ቁ. 909/33፣ አዲስ አበባ፣
ገብረየሱስ ሕንፃ 5ኛ ፎቅ፣ የቢ.ቁ. 59፣ መቐለ